# ማህበረሰብ መር የተፋጠነ የውሃ'ንጽህናና ሀይጅን ፕሮጀክት (ኮዋሽ)
# ምእራፍ ሶስት

Community Managed Project Approach

CMP

Effective and sustainable
WaSH services

## ለማህበረሰብ መር የፕሮጀክት ትግበራ የሚያገለግል የውሃ' ንጽህናና ሀይጅን ኮሚቴ የእቃዎች' የአገልግሎቶችና የስራዎች ግዥ መመሪያ

**ህዳር 29/2009**

**<u>አዲስ አበባ</u>**

## ማውጫ


1. መግቢያ ....1

2. በአለፉት የኮዋሽ ፕሮጀክት ምእራፎች የነበረው የዋሽኮ የገዥ መመሪያ መከለስ ለምን አስፈለገ ....1

3. ይህ የግዥ መመሪያ ተግባራዊ የሚሆንባቸው የውሃና ንጽህና ፕሮጀክቶች ....1

4. በዚህ የግዥ መመሪያ ውስጥ የተካተቱ ግዥዎች ትርጉም ....2

4.1 የእቃዎች ግዥ ....2

4.2 የአገልግሎት ግዥ (ለግንባታ የሚያስፈልገውን የባለሙያ ጉልበት) እና የሌሎች አገልግሎቶች ግዥ ....2

4.3 የስራዎች ግዥ/ሙሉ የግንባታ ስራዎች ግዥ ....2

5. በዚህ የግዥ መመሪያ ተቀባይነት ያላቸው አቅራቢዎች' አገልግሎት ሰጪዎችና የግንባታ ተቋራጮች ....3

5.1 ለእቃዎችና ለሌሎች አገልግሎቶች ግዥ....3

5.2) ለግንባታ የሚያስፈልግ የጉልበት ግዥ ....3

5.3) የስራዎች ግዥ/የሙሉ የግንባታ ስራዎች ግዥ ....4

6. በኮዋሽ ፕሮጀክት በማህበረሰብ ሊፈጸሙ የተፈቀዱ/የሚተገበሩ የግዥ ዘዴዎች....4

6.1 ስለ ግዥ ዘዴዎቹ አጠቃላይ ጉዳዮች....4

6.2) የእቃዎች' የግንባታ ጉልበትና ሌሎች አገልግሎቶች ግዥ ....5

6.2.1) **ከአንድ አቅራቢ የሚፈጸም ግዥ** ....5

6.2.1.1) የግንባታ ፈቃድ ለሌላቸው አርቴፕኖች የግንባታ የጉልበት ግዥ ላይ ማሳተፍ....6

6.2.1.2) ቀድሞ በተዘጋጀ የቁርጥ የግንባታ ነጠላ ዋጋን በመጠቀም የግንባታ ጉልበት ውል አሰጣጥ ....6

6.2.2) በመወዳደሪያ ሀሳብ መመየቂያ የሚፈጸም ግዥ ....7

6.2.1) ግልጽ ጨረታ....7

6.3) የስራዎች ግዥ/የሙሉ የግንባታ ስራዎች ግዥ ....8

6.3.1) ከአንድ አቅራቢ የሚፈጸም ግዥ ....8

6.3.2) በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ የሚፈጸም ግዥ ....9

6.3.3) የግልጽ ጨረታ ግዥ....9

6.3.3.1) ስለግልጽ ጨረታ ግዥ ተጨማሪ ጉዳዮች ..........10

7. በውክልና የሚፈጸሙ ግዥዎች ..........12

8. ከግንባታ የተረፉ እቃዎችን እንደ ስሚንቶና ፌሮ የመሳሉትን ስለመሸጥ ..........12

## 1. መግቢያ

የኮዋሽ ፕሮጀክት ምእራፍ 1 እና 2 የወረዳዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በ2008 የበጀት ዓመት 76 ደርሶ ነበር፡፡ ለሶስት ዓመታት የሚቆይ የፕሮጀክቱ ሶስተኛ ምእራፍ ከነሀሴ 2008 ዓ.ም ጀምሮ በነበሩት 76 ወረዳዎች ላይ በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡ ለአለፉት 5 ዓመታት የውሃ ንጽህናና ሀይጅን ኮሚቴዎች (ዋሽኮዎች) ይጠቀሙበት የነበረው የግዥ መመሪያ ያልተቀየረ ነበር፡፡ በዚህ የግዢ መመሪያ ክፍል ሁለት ላይ በተጠቀሱት የተለያዩ ምክንያቶች የግዥ መመሪያው ለሶስተኛው ምእራፍ አጠቃቀም በሚያመች መልኩ መከለስ በማስፈለጉ ይህ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡ የግዥ መመሪያው በመጀመሪያ በፌደራል ኮዋሽ ፕሮጀክት የተዘጋጀ ቢሆንም የኮዋሽ ፕሮጀክት ክልሎች የድጋፍ ሰጪ ቡድን አባላት ከሚመለከታቸው የሴክተር መ/ቤት ባለሙያዎች ጋር በመወያየት በተጨማሪ ሃሳቦች የዳበረ መመሪያ ነው፡፡

## 2. በአለፉት የኮዋሽ ፕሮጀክት ምእራፎች የነበረው የዋሽኮ የገዥ መመሪያ መከለስ ለምን አስፈለገ

በአለፉት የኮዋሽ ምእራፎች ጥቅም ላይ ይውል የነበረው የዋሽኮ የገዥ መመሪያ መከለስና ይህን አዲስ መመሪያ ማዘጋጀት ያስፈለገው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው፡፡

- <u>በየጊዜው እየጨመረ በመጣው</u> የዋና ዋና የግንባታ ቁሳቁሶችና መሳሪያዎች ዋጋ የተነሳ ዋሽኮዎች ግዥዎችን በቀላሉና በተቀላጠፈ ሁኔታ ማከናወን እንዲችሉ የግዥ ጣሪያዎችን ከፍ ማድረግ በማስፈለጉ'
- በፕሮጀክቱ ምእርፍ 2 ማጠለቂያ አካባቢ በፕሮጀክቱ የታቀፉ አንዳንድ ኪስ ወረዳዎች (ከዋና መንገድ ብዙ የራቁ ወረዳዎች) ለምሳሌ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ወረዳዎች በግዥው መመሪያ ላይ በተቀመጠው የፕሮፎርማ ግዥ ዘዴ ለመጠቀም በቂ አቅራቢዎች ማግኘት አስቸጋሪ በመሆኑ <u>የቀጥታ ግዥ ጣሪያን ከፍ ማድረግ/ማሻሻል</u> በማስፈለጉ'
- የማህበረሰብ ፕሮጀክት ትግበራ አሰራር መጀመሪያ ሲነደፍ የነበረው ዋና ታሳቢ ዋሽኮዎች የአርቴዣን ጉልበትንና የግንባታ ቁሳቁሶችን በተናጠል በመግዛት ይጠቀማሉ በሚል ታሳቢ ቢሆንም በአለፉት ምእራፎች የታየው ልምድ ግን ዋሽኮዎች የግንባታ ስራዎችን ሙሉ ግንባታ ውል በመስጠት የማሰራት ፍላጎት እየጨመረ በመምጣቱ <u>የሙሉ ውል የግዥ ሂደትን</u> በዝርዝር ማስቀመጥ በማስፈለጉ'
- በአለፉት ምእራፎች ለቀላል የውሃ አቅርቦት ቴክኖሎጊዎችና ለከፍተኛ የውሃ አቅርቦት ቴክኖሎጂዎች (low and high tech water supply schemes) አገልግሎት ላይ እንዲውሉ የተዘጋጁት የግዥ መመሪያዎች የተለያዩ ስለነበሩ ይህም አንዳንድ ጊዜ በአጠቃቀም ወቅት ግርታን ስለሚፈጥሩ እንዲሁም እነዚህን የግዥ መመሪያዎች ለመጠቀም በምንጮችና በሰበት ሀይል ለሚሰሩ የውሃ ማከፋፈያ መስመሮች መካከል ግልጽ የሆነ የፍቺ ልዩነት (ወሰን) ባለመኖሩ <u>ለቀላልና ከፍተኛ ቴክኖሎጂዎች</u> ወጥ የሆነ የግዥ መመሪያ መጠቀም በማስፈለጉ'
- በምእራፍ 1 እና 2 አገልግሎት ላይ የነበረው የግዥ መመሪያ ዋሽኮዎች ግዥዎችን በግልጽ ጨረታ እንዴት ማከናወን እንደሚችሉ ዝርዝር አቅጣጫዎችን ያላስቀመጠ ስለነበርና ዋሽኮዎች ግዥን በግልጽ ጨረታ ማከናወን በሚኖርባቸው ወቅት ማከናወን እንዲችሉ የግልጽ ጨረታ አፈጻጸምን በዝርዝር ማስቀመጥ በማስፈለጉ'
- በምእራፍ 1 እና 2 አገልግሎት ላይ የነበረው የግዢ መመሪያ <u>ከግንባታ ሊተርፉ የሚችሉ ዋና ዋና ቀሳቁሶችን</u> ዋሽኮዎች እንዴት እንደሚሸጡ ያላካተተ መሆኑ ከለሳው ማድረግ ካስፈለገባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች ናቸው፡፡

## 3. ይህ የግዥ መመሪያ ተግባራዊ የሚሆንባቸው የውሃና ንጽህና ፕሮጀክቶች

ይህ የግዥ መመሪያ አገልግሎት ላይ የሚውለው በኮዋሽ ፕሮጀክት የበጀት ድጋፍ በዋሽኮዎች ለሚተገበሩ/ለሚገነቡ የመጠጥ ውሃና የተቋማት መጸዳጃ ቤቶች ግንባታዎች ነው፡፡ በዚህ መመሪያ የሚተገበሩት የፕሮጀክቶች ዝርዝር የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ) **የመጠጥ ውሃ ተቋማት**

- አዲስ የሚገነቡ ወይም የመልሶ ግንባታ/ከባድ ጥገና የሚያስገልጋቸው እጅ ፓምፕ የሚገጠምላቸው የእጅ ጉድጓዶች
- አዲስ የሚገነቡ ወይም የመልሶ ግንባታ/ከባድ ጥገና የሚያስገልጋቸው በቦታው ወይም ከማጠራቀሚ ጋን ጋር የሚገነቡ ምንጮች
- ለተቋማት አገልግሎት የሚውሉ የጣራ ውሃ ማሰባሰብ ግንባታ
- አዲስ በማሽን የሚቀፈሩና የእጅ ፓምፕ የሚገጠምላቸው መለስተኛ ጥልቅ ጉድጓዶች
- አዲስ የሚገነቡ ወይም የመልሶ ግንባታ/ከባድ ጥገና የሚያስገልጋቸው በሰበት ሀይል ከሚሰሩ ምንጮች የውሃ ማከፋፈያ ስራዎች
- አዲስ የሚገነቡ ወይም የመልሶ ግንባታ/ከባድ ጥገና የሚያስገልጋቸው በሞተር ሀይል ከሚሰሩ ምንጮች የውሃ ማከፋፈያ ስራዎች
- አዲስ በማሽን የሚቆፈሩና ለውሃ ማከፋፈያ ግንባታ የሚውሉ ጥልቅ ጉድጓዶች ቁፋሮ

- አዲስ የሚገነቡ ወይም የመልሶ ግንባታ/ከባድ ጥገና የሚያስገልጋቸው ከጥልቅ ጉድጓዶች የውሃ ምንጭነት ያላቸው የውሃ ማከፋፈያ ስራዎች

**ለ) የተቋማት መጸዳጃ ቤቶች**

- ለትምህርት ቤቶች አገልግሎት የሚሰጡ አዲስ የመጸዳጃ ቤቶች ግንባታ
- ለጤና ተቋማት አገልግሎት የሚሰጡ አዲስ የመጸዳጃ ቤቶች'የእትብት መቅበሪያ ጉድጓድና የቆሻሻ ማቃጠያ ግንባታ

# 4. በዚህ የግዥ መመሪያ ውስጥ የተካተቱ ግዥዎች ትርጉም

ከዚህ በፊት በተገኘው የውሃ ተቋማትና የመጸዳጃ ቤቶች ግንባታ ልምድ በመነሳት ለውሃ ጣቢያና የተቋማት መጸዳጃ ቤቶችን ግንባታ ለማከናወን አገልግሎት የሚውሉት ግዥዎች ትርጉም እንደሚከተለው ተገልጾዋል፡፡

## 4.1 የእቃዎች ግዥ

የእቃዎች ግዥ የምንለው ለውሃ ጣቢያም ሆነ ለተቋማት መጸዳጃ ቤቶች ግንባታ የሚየስፈልጉ በአካባቢ የሚገኙም ሆኑ የኢንዱስትሪ ውጤቶች የሆኑ የግንባታ ቁሳቁሶችና የግንባታ ማሳሪያዎችችን ግዥ ሲከናወን ነው፡፡ እነዚህም ቁሳቁሶችና መሳሪያዎቸ በዋነኛነት የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

- አሸዋ' ስሚንቶ' ፌሮ' ፎርምወርክ' ፓፕም' ጀኔሬተርና የመሳሰሉት ግዥ'
- የግንባታ መሳሪያዎች እንደ ባልዲ' ዶማ' አካፋ' የአደጋ መከላከያ ባርኔጣ' ናይለን ገመድና መዶሻ የመሳሰሉትን ግዥ ያካትታል፡፡

የእቃዎች ግዥ ማህበረሰቡ በግንባታ ወቅት ለማቅረብ ቃል የገባውን የግንባታ ቁሳቁስና መሳሪያዎችን አያካትትም፡፡

ዋሽኮዎች ይህን ግዥ ዘዴ በመጠቀም የግንባታ ቁሳቁሶችንና መሳሪያዎችን ሲገዙ ለግንባታ የሚያስፈገልገውን የባለሙያ ጉልበትና ሌሎች አገልግሎቶችን ግዥ በተናጠል በማከነወን ግንባታው እንዲከናወን ያደርጋሉ፡፡

## 4.2 የአገልግሎት ግዥ (ለግንባታ የሚያስፈልገውን የባለሙያ ጉልበት) እና የሌሎች አገልግሎቶች ግዥ

የአገልግሎት ግዥ (ለግንባታ የሚያስፈልገውን የባለሙያ ቅጥር) እና የሌሎች አገልግሎቶች ግዥ የምንለው ለውሃ ጣቢያና ለመጸዳጃ ቤቶች ግንባታና ከባድ ጥገና የሚያገለግል የባለሙያ ቅጥርና ሌሎች አገልሎቶችን ግዥ ነው፡፡

የባለሙያ ቅጥር/የባለሙያ የጉልበት ግዥ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡፡

- የውሃ ጣቢያና የመጸዳጃ ቤቶች ግንባታ ለግል ተቋራጮች' ለጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶች ' ለአርቴገገን ማህበራት እንዲሁም ለግለሰብ አርቴገኖች የጉልበት ዋጋ ውል መስጠትን ናቸው፡፡

የሌሎች አገልግሎቶች ግዥ  የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡፡

- ለግንባታ የሚያስፈለጉ ማሳሪዎችን መከራየት (ለምሳሌ የፎርም ወከር ጣወል/ፓናል መከራየት)'
- የሚገዙት የግንባታ ቁሳቁሶችና መሳሪያዎች ግዥ የማጓጓዛ ዋጋ ካልጨመረ የግንባታ ቁሰቁሶችንና መሳሪያዎችን ለማጓጓዝ የሚደረግ ትራንስፓርት አገልግሎት ግዥ ናቸው፡፡

የአገልግሎት ግዥ ማህበረሰቡ በግንባታ ወቅት ለማቅረብ ቃል የገባውን የጉልበት አስተዋጾ አያካትትም፡፡

ዋሽኮዎች ይህን ግዥ በመጠቀም የግንባታ የሚውሉ የባለሙያ ጉልበትና ሌሎች አገልግሎቶችን ሲገዙ ለግንባታ የሚያስፈገልገውን የግንባታ ቁሳቁሶችንና መሳሪያዎችን ግገር በተናጠል በማከነወን ግንባታው እንዲከናወን ያደርጋሉ፡፡

## 4.3 የስራዎች ግዥ/ሙሉ የግንባታ ስራዎች ግዥ

የስራዎች ግዥ/ሙሉ የግንባታ ስራዎች ግዥ የምንለው የግል ተቋራጮች' አነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት እና የአርቴገገን የግንባታ ማህበራት ለግንባታ የሚያስፈልገውን አብዛኛውን ወይም ሁሉንም የሰው ሀይል' የግንባታ ቁሳቁሶችና መሳሪያዎችን በማቅረብ የማህበረሰብ የመጠጥ ውሃ ተቋማትን ግንባታና ከባድ ጥገና እንዲሁም የተቋማት መጸዳጃ ቤቶችን ግንባታ እንዲያከናውኑ ውል ስንሰጥ ነው፡፡

ይህ ግዥ ማህበረሰቡ በግንባታ ወቅት ለማቅረብ ቃል የገባውን የግንባታ ቁሳቁሶችና መሳሪያዎች እንዲሁም የጉልበት አስተዋጾን አያካትትም፡፡

# 5. በዚህ የግዥ መመሪያ ተቀባይነት ያላቸው አቅራቢዎች' አገልግሎት ሰጪዎችና የግንባታ ተቋራጮች

## 5.1 ለእቃዎችና ለሌሎች አገልግሎቶች ግዥ

**ለእቃዎችና ለሌሎች አገልግሎቶች ግዢ ተቀባይነት ያላቸው የሚከተሉት አቅራቢዎች ናቸው፡፡**

- ለእቃዎች (የኢንዱስትሪ ውጤት ለሆኑ የግንባታ ቁሳቁሶችና መሳሪያዎች) ግዥ
    - በዘመኑ የታደሰ የግግድ ፈቃድና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ያላቸው እንዲሁም በአቅራቢዎች ዝርዝር የተመዘገቡ የእቃ አቅራቢዎች፡፡ የወረዳው ፋይናንስ ጽ/ቤት የትኞቹ አቅራቢዎች በአቅራቢዎች ዝርዝር እንደተመዘገቡ ለዋሽኮዎች መረጃ ይሰጣል፡፡
- የኢንዱስትሪ ውጤት ያልሆኑ/በአካባቢ የሚገኙ የግንባታ ቁሳቁሶች ግዢ
    - እንደወረዳው ተጫባጭ ሁኔታ አሸዋ' ድንጋይ እና እንጨት ንግድ ፈቃድ ከሌላቸው አቅራቢዎች መግዛት ይቻላል፡፡
- የትራንስፖርት/የመጓጓዣ አገልግሎት ግዥ
    - የጋማ ከብቶችንና ጋሪን ለትራስፖርት አገልግሎት ፈቃድ ከሌላቸው ግለሰቦች መከራየት ይቻላል፡፡
    - እንደወረዳው ተጨባጭ ሁኔታ ንግድ ፈቃድ ያላቸው የትረንስፖረት አገልግሎት የሚሰጡ መኪናዎች ከሌሉና ይህም በወረዳው የዋሽ ቡድን የሚረጋገጥ ከሆነ ለግንባታ እቃዎችና መሳሪያዎች ማጓጓዣ የሚሆን የመኪና አገልግሎትን ፈቃድ ከሌላቸው ግለሰቦች መግዛት/መከራየት ይቻላል፡፡

## 5.2) ለግንባታ የሚያስፈልግ የጉልበት ግዥ

**ለውሃ ተቋማት ግንባታ ስራ ለሚያስፈልግ ባለሙያ የጉልበት ግዢ ተቀባይነት ያላቸው የሚከተሉት ናቸው፡፡**

- በውሃ ስራ ግንባታ ፈቃድ ያላቸው የግል ተቋራጮች
- የጉድጓድ ቁፋሮ ተቋራጮች
- በውሃ ስራ ግንባታ ፈቃድ ያላቸው የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት
- በውሃ ስራ ግንባታ ፈቃድ ያላቸው የአርቴዣን ማህበራት
- በውሃ ስራ ግንባታ ፈቃድ ያላቸው ግለሰብ አርቴዣኖች
- በውሃ ጣቢያ ግንባታ የሰለጠኑና በውሃ ቢሮ ወይም በዞን ውሃ መምሪያዎች ወይም በወረዳ የውሃ ጽ/ቤቶች አውቅና ያገኙ ነገር ግን በተለያዩ ምክንያቶች የግንባታ ፈቃድ የሌላቸው አርቴዣኖች በዚህ የግዥ መመሪያ ንኡስ ክፍል 6.2.1.1 ላይ የተቀመጠው ሁኔታ መሰረት የግንባታ ጉልበት ግዥ ላይ ሊሳተፉ ይችላሉ፡፡

**ለተቋማት መጸዳጃ ቤቶች ግንባታ ስራ ለሚያስፈልግ ባለሙያ የጉልበት ግዥ ተቀባይነት ያላቸው የሚከተሉት ናቸው፡፡**

- የህንጻ ግንባታ ተቋራጮች
- በህንጻ ግንባታ ፈቃድ ያላቸው የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት
- በመጸዳጃ ቤት ግንባታ ፈቃድ ያላቸው የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ካሉ
- በተቋማት መጸዳጃ ቤቶች ግንባታ የሰለጠኑ ወይም ስልጠና ሳይወስዱ ስራውን የመስራት ልምድ ያላቸው ወይም ስራውን ለመስራት ብቃት ይኖራቸዋል ተብሎ የሚታመንባቸው አዝቴዣኖች ነገር ግን የግንባታ ፈቃድ የሌላቸው አርቴዣኖች በዚህ የግዢ መመሪያ ንኡስ ክፍል 6.2.1.1 ላይ የተቀመጠው ሁኔታ መሰረት የግንባታ ጉልበት ግዥ ላይ ሊሳተፉ ይችላሉ፡፡

## 5.3) የስራዎች ግዥ/የሙሉ የግንባታ ስራዎች ግዥ

**ለውሃ ተቋማት ግንባታ የስራዎች ግዥ/የሙሉ የግንባታ ስራዎች ግዥ ተቀባይነት ያላቸው ተቋራጮች የሚከተሉት ናቸው::**

- በውሃ ስራ ግንባታ ፈቃድ ያላቸው የግል ተቋራጮች
- የጉድጓድ ቁፋሮ ተቋራጮች (ለጉድጓድ ቁፋሮ' ኬዚንግ ማቅረብና ማስገባት ብቻ ወይም/እና የጉድጓድ እናት ግንባታና እጅ ፓምፕ አቀርቦ መትከል ሊሆን ይችላል)
- በውሃ ስራ ግንባታ ፈቃድ ያላቸው የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት
- በውሃ ስራ ግንባታ ፈቃድ ያላቸው የአርቴፃን ማህበራት
- በውሃ ስራ ግንባታ ፈቃድ ያላቸው ግለሰብ አርቴፃኖች

**ለተቋማት መጸዳጃ ቤቶች ግንባታ የስራዎች ግዢ/የሙሉ የግንባታ ስራዎች ግዢ ተቀባይነት ያላቸው ተቋራጮች የሚከተሉት ናቸው::**

- የህንጻ ግንባታ ተቋራጮች
- በህንጻ ግንባታ ፈቃድ ያላቸው የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት
- በመጸዳጃ ቤት ግንባታ ፈቃድ ያላቸው የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ካሉ

# 6. በኮዋሽ ፕሮጀክት በማህበረሰብ ሊፈጸሙ የተፈቀዱ/የሚተገበሩ የግዥ ዘዴዎች

## 6.1 ስለ ግዥ ዘዴዎቹ አጠቃላይ ጉዳዮች

በማህበረሰብ ፕሮጀክት ትግበራ (ሲ.ኤም.ፒ) አሰራር ለዋሽኮዎች የተፈቀዱ የግዢ ዘዴዎች በአጠቃላይ የኢትዮጲያ ፌዴራላዊ መንግስት የግዥ እና ንብርት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2009 እና በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስተር እ.ኤ.አ ሰኔ 2010 የተዘጋጀው የመንግስት የግዥ መመሪያ መሰረት ያደረገ ነገር ግን የዋሽኮ አባላት ስራ መደበኛ ኑሮአቸውን ለመምራት ከሚሰሩት ስራ ላይ ተጨማሪ በመሆኑና የዋሽኮዎችን የማስፈጸም አቅም ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ የተወሰኑ ለውጦች/ማሻሻያዎች የተደረጉበት ነው::

ዋሽኮ ማለት የውሃ' ንጽህናና ሀይጅን ኮሚቴን ለመግለጽ የምንጠቀምበት ምህጻረ ቃል ሲሆን ይህም የውሃ ጣቢያቸውን ግንባታ ለማቀድ' ለማስፈጸም (ግዥንና የገንዘብ አስተዳደርን ጨምሮ) እንዲሁም የውሃ ተቋሙ ከተገነባ በኋላ ለማስተዳደር በተጠቃሚው ማህበረሰብ የተመረጡ የኮሚቴ አባላት ናቸው:: በትምህርት ተቋማት ላይ ለሚገነቡ የውሃ ተቋማትና የመጸዳጃ ቤቶች ግንባታና ማስተዳደር እንደዋሽኮ ሁኖ የሚያገለግለው ኮሚቴ የወላጅ መምህር ህብረት ሲባል በጤና ተቋማት ላይ ያለው ኮሚቴ ደግሞ የጤና ኮሚቴ ይባላል::

በዚህ የግዥ መመሪያ መሰረት ለእቃዎች' ለአገልግሎቶችና ለስራዎች/ለሙሉ የግንባታ ውል ግዥዎች በዋሽኮዎች እንዲተገበሩ የተፈቀዱ ሶስት የግዥ ዘዴዎች የሚከተሉት ናቸው::

- ግልጽ ጨረታ'
- በመወዳደሪያ ሀሳብ መመየቂያ/በፕሮፎርማ የሚፈጸም ግዥ'
- **ከአንድ አቅራቢ የሚፈጸም ግዥ ናቸው::**

በዚህ የግዥ መመሪያ ውስጥ እያንዳንዱ ለዋሽኮዎች የተፈቀደ የግዥ ዘዴ ሊተገበርበት የሚችለው የግዥው ዋጋ ጣሪያና ሌሎች መሟላት የሚገባቸው ሁኔታዎች በሚመለከተው የግዥ ዘዴ ውስጥ ለማካተት ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል:: በዚህ መመሪያ ላይ ያልተካተቱ ነገር ግን ለእንዳንዱ የተፈቀደ ግዥ አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮች ሲገጥሙ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስተር እ.ኤ.አ ሰኔ 2010 የተዘጋጀው የመንግስት የግዥ መመሪያ ክልሎች እንደየተጨባጭ ሁኔታቸው በማሻሻልና ወደየክልሉ የስራ ቋንቋ በመተርጎም ለየወረዳዎቹ ፋይናንስ ጽ/ቤቶች የላኩ ስለሆነ ይህን መመሪያ በመጠቀም የጎደሉትን አስፈላጊ ሁኔታዎች ለማሟልት መጠቀም ይቻላል::

ይህ የግዥ መመሪያ ሲዘጋጅ የሚከተሉትን የመንግስት የግዥ መርሆችን መሰረት ያደረገ ሲሆን የመመሪያው አጠቃቀምም እነዚህን መርሆች

ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

- በግዢ አፈጻጸም ረገድ የመንግስት ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማስገኘት'
- ማናኛውም ግዥ የሚከናወነው በታቀደና በግልጽ ጨረታ ዘዴ እንዲሆን ይፈለጋል፡፡ ነገር ግን በዚህ መመሪያ የተቀመጡት ሁኔታዎች ሲሟሉ/ሲያስገድዱ ብቻ ሌሎቹ የግዥ ዘዴዎች (በመወዳደሪያ ሀሳብ መመየቂያ የሚፈጸም ግዥ ወይም **ከአንድ አቅራቢ የሚፈጸም ግዥ** )ተግባራዊ ሊደረጉ ይችላሉ፡፡

- በኢትዮጲያ ለተመረቱ እቃዎች እንዲሁም በአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት አዋጆች የተቋቋሙ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት በመንግስት የግዥ አዋጅና መመሪያ ላይ የተቀመጡትንና ሊደረጉላቸው የሚገቡትን ተጨማሪ ልዩ አስተያየቶች ማድረግ፡፡

- መንግስት ባወጣው የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ መሰረት የግዥ ዋጋቸው ብር 100000 /አንድ መቶ ሺህ/ እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ማንኛውም አይነት ግዥዎች የሚወዳደሩት እጩዎች የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢዎች ብቻ ናቸው፡፡

- አንዳንድ በአካባቢ የሚገኙ የግንባታ ቁሳቁሶች እንደ አሸዋ' ድንጋይ እንጨት ግዥዎች እንዲሁም አንዳንድ አገልግሎቶች ግዥዎች ለምሳሌ የጋሪና ሌሎች የጋማ ከብቶች የትራንፖርት ኪራዮች እንዲሁም የግንባታ ፈቃድ ላላወጡ አርቴጘኖች በስተቀር ለሁሉም ግዥዎች ለመሳተፍ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ሊኖራቸው ይገባል፡፡

- ዋሽኮዎች ከአንድ አቅራቢ ግዥን ለመፈጸም ብለው ብቻ በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ወይም በግልጽ ጨረታ የሚፈጸም ግዥን ለመሸሸ ሲባል በአንድ ጊዜ ሊገዙ የሚችሉ ግዥዎችን መከፋፈል የለባቸውም፡፡

- ማንኛውም የግዥ ውሳኔ በሚሰጥበት ወቅት (ለምሳሌ የግዥ ዘዴ በሚመረጥበት ወቅት አሸናፊው ተጫራች በሚለይበት ወቅት) ውሳኔው ለሚመለከታቸው ሁሉ ግልጽ እና በቃለጉባኤ መደገፍ አለበት፡፡

- ከመወዳደሪያ መስፈርቶች ጋር ባልተያያዙና ሌሎች ምክንቶች ለምሳሌ ከጾታ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች በዕጩ ተቀዳዳሪዎች መካከል አድልኦ አለማድረግ ናቸው፡፡

ይህ የግዥ መመሪያ በየክልሉ ገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ቢሮዎች በመጽደቅ ለኮዋሽ ፕሮጀክት ለማህበረሰብ ፕሮጀክት ትግበራ (ሲ.ኤም.ፒ) አሰራር አገልግሎት እንዲውል በመግለጽ ቢሮው ለወረዳው ገንዘብ ጽ/ቤት ይልካል፡፡ ገንዘብ ጽ/ቤቱ ደግሞ ለውሃ' ለጤናና ለትምርህርት ጽ/ቤቶች ይሠጣል፡፡

## 6.2) የእቃዎች' የግንባታ ጉልበትና ሌሎች አገልግሎቶች ግዥ

### 6.2.1) **ከአንድ አቅራቢ የሚፈጸም ግዥ**

የእቃዎች' የግንባታ ጉልበትና ሌሎች አገልግሎቶችን ከአንድ አቅራቢ ግዥ መፈጸም የሚቻለው የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ ነው፡፡

- **በአንድ ጊዜ የሚገዛው እቃ' የግንባታ ጉልበት ወይም አገልግሎት ዋጋ ግምት ብር 10,000 እና ከዚያ በታች ሲሆን'**

- **በአንድ ጊዜ የሚገዛው እቃ' የግንባታ ጉልበት ወይም አገልግሎት ዋጋ ግምት ከብር 10,000 በላይ ሁኖ ነገር ግን ከሚከተሉት ሁኔታዎች ቢያንስ አንዱ ሲያጋጥምም** ከአንድ አቅራቢ ግዥ ዘዴን መጠቀም ይቻላል፡፡ በዚህ ጊዜ ዋሽኮው በሁኔታዎቹ ላይ በመወያየት ውሳኔውን በቃለ ጉባኤ መያዝ አለበት፡፡

  - በመወዳደሪያ ሀሳብ መመየቂያ የሚፈጸም ግዥ **ቢያንስ ሁለት ጊዜ ተሞክሮ** በቂ ተወዳደሪ ያልተገኘ ወይም ፕሮፎርማውን ሞልተው የመለሱ እጩ ተወዳዳሪዎች የገዥውን ፍላጎት ማማላት ሳይችሉ'

  - ዕቃው የሚገኘው ከአንድ የተለየ አቅራቢ ብቻ ሲሆን ወይም እቃውን ለማቅረብ አቅራቢው ብቸኛ መብት ያለውና ለእቃው ሌላ አማራጭ ወይም ትክ ሳይኖረው ሲቀር አቅራቢው እቃውን በሚፈለገው ጥራት' ወቅታዊ በሆነ/ተቀባይነት ባለው ዋጋና በሚፈለገው ጊዜ ማቅረብ የሚችል ሲሆን'

  - የእቃው ወይም የአገልግሎቱ ግዥው በአስቸኳይ ካልተፈጸመና ስራው ከተጓተተ በፕሮጀክቱ ላይ ከፍተኛ ችግርና ጉዳት የሚያስከትል መሆኑ ሲታመንበት፡፡ ለምሳሌ በአካባቢው ስራው ላይ አደጋ ሊስከትል የሚችል ከፍተኛ ዝናብ መከሰት፡፡

- በቴክኒክ ምክንያት እቃዎችና አገልግሎቶች ከአንድ ግለሰብ ወይም ድርጅት ብቻ የሚቀርቡ ከሆነና የዚህ ግለሰብ ወይም ድርጅት ጥራትና የቴክኒክ ችሎታው ከሌሎች በተመሳሳይ መስክ ከሚሰሩ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ መሆኑ ሲታመንበትና ግለሰቡ ወይም ድርጅቱ እቃውን ወይም አገልግሎቱን በሚፈለገው ጥራትና ተቀባይነት ባለው የገበያ ዋጋ ማቅረብ እንደሚችል ሲታመንበት'

**ከአንድ አቅራቢ ግዥ በሚፈጸምበት ወቅት ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ሌሎች ጉዳዮች**

- በአቅራቢው የሚቀርቡት እቃዎች ጥራት' አገልግሎት የሚሰጠው የስራ ተቋራጭ ወይም አርቴዣኑ የቴክኒክ ብቃት' እቃው ወይም የአገልግሎቱ የሚቀርብበት ዋጋ አግባብነት የመሳሰሉት ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው፡፡

- የወራዳው ዋሽ ቡድን/የወረዳው ውሃ ጽ/ቤት በየጊዜው የገበያ ጥናት  በማድረግ ለዋሽኮው ውሳኔ የሚያግዝ የአገልግሎቶችና እቃዎችን ዋጋ መረጃ መስጠት ያስገልጋል፡፡

- ለግንባታ የሚያስፈልገውን ጉልበት ለአርቴዣኖች' ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ወይም ለሌሎች የስራ ተቋራጮች ውል በምንሰጥበት ወቅት የወረዳው ውሃ ጽ/ቤት ከክልሉ ውሃ ቢሮ ጋር በመተባበር ለጉልበት ዋጋ ውል ክፍያ የሚያገለግል የክፍያ መመሪያ በማዘጋጀት ዋሽኮዎች ውል በሚሰጡበት ጊዜ በቀጥታ ለመዋዋል ወይም በአገልግሎት ሰጪው የሚቀርበውን ዋጋ አግባብነት ለማየት እንዲጠቀሙበት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በዚሁ አግባብ የትምህርትና ጤና ቢሮዎች /ጽ/ቤቶች በትምህርትና በጤና ተቋማት ላይ ለሚገነቡት መጸዳጃ ቤቶች የዋጋ ግምት ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል፡፡

- ዋሽኮው ፍላጎቱን የሚገልጽ መግለጫና የሚገዛውን እቃ ወይም አገልግሎት ጥራት መግለጫ' ብዛት' የማቅረቢያ ጊዜና ሌሎች ሁኔታዎች የሚያብራራ የዋጋ መሙሊያ ሰነድ ማዘጋጀት አለበት፡፡

- ዋሽኮዎች ዋጋን ቀጥታ ከአንድ ተጫራች መጠየቅና ከተጫራቹ ጋር <u>በዋጋና</u> ሌሎች የውል ሁኔታዎች ላይ (ለምሳሌ የውል ማጠናቀቂ ጊዜ) በነጻነት/በግልጽ መደራደር ይችላሉ፡፡

## 6.2.1.1) የግንባታ ፈቃድ ለሌላቸው አርቴዣኖች የግንባታ የጉልበት ግዥ ላይ ማሳተፍ

በግንባታ ስራ የሚሰማሩ ድርጅቶች መብትና ግዴታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ለማድረግና የሀገሪቱን የግብር መሰረት ለማስፋት መንግስት ለተለያዩ በግንባታ ስራ ላይ የተሰማሩ ግለሰቦችን በግል የግንባታ ፍቃድ ወይም በማህበር በመደራጀት የግንባታ ፈቃድ እንዲያወጡ ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ነው፡፡ በፕሮጀክቱ ወረዳዎች በፕሮጀክቱና ከዚህ በፊት በሌሎች የሰለጠኑ አርቴዣኖች ይገኛሉ፡፡ ነገር ግን አርቴዣኖችን በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋምነት ለማደራጀት ጊዜ ስለሚወስድ አብዛኛዎች አርቴዣኖች የግንባታ ፈቃድ የላቸውም፡፡ እነዚህንም አርቴዣኖች ለግንባታ አለመጠቀም የግንባታ ፈቃድና ልምድ ያላቸው ተቋራጮች ከማግኘት ችግር የተነሳ በአብዛኛዎቹ ወረዳዎች የታቀዱት የመጠጥ ወሃና የመጸዳጃ ቤት ስራዎች ላይከናወኑ የሚችሉበት አደጋ ሰፊ ነው፡፡ ስለዚህ ያልተደራጁ አርቴዣኖችን በማህበራት እንዲደረጁ ከማትጋትና ከማገዝ በተጨማሪ እነዚህን አርቴዣኖች በሚከተሉት ሁኔታዎች ለግንባታና ለከፍተኛ ጥገና ስራዎች ማሰማራት ያስፈልጋል፡፡

ሀ) በውሃ ጣቢያ ግንባታ የሰለጠኑት አርቴዣኖች ለእጅ ጉድጓድ' ለምንጭና ለውሃ ማከፋፈያ መስመር ግንባታ በአንድ ጊዜ እስከ ብር 10,000 የሚደርስ የጉልበት ዋጋ ቀጥተኛ ግዥ ላይ ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡ እንዱሁም በመጸዳጃ ቤት ግንባታ የሰለጠኑ አርቴዣኖች ወይም ስልጠና ሳይወስዱ ስራውን የመስራት ልምድ ያላቸው ወይም ስራውን ለመስራት ብቃት ይኖራቸዋል ተብሎ የሚታመንባቸው አዝቴዣኖች በተቋማት ላይ ለሚሰሩ የመጸዳጃ ቤቶች ግንባታ ላይ ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡

ለ) በውሃ ጣቢያ ግንባታ የሰለጠኑት አርቴዣኖች ማንኛውንም የጉልበት ዋጋ ግምት ያላቸው አስቀድሞ በተዘጋጀና ወጥ የሆነ የጉልበት ዋጋ ክፍያ መመሪያ ወይም አርቴዣን የጉልበት ዋጋ የክፍያ መመሪያ በሚሰሩ የእጅ ጉድጓድ' የምንጭና የውሃ ማከፋፈያ መስመር ስራዎች ላይ ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡ እንዱሁም በመጸዳጃ ቤት ግንባታ የሰለጠኑ ወይም ስልጠና ሳይወስዱ ስራውን የመስራት ልምድ ያላቸው ወይም ስራውን ለመስራት ብቃት ይኖራቸዋል ተብሎ የሚታመንባቸው አርቴዣኖች በተቋማት ላይ በሚሰሩ የመጸዳጃ ቤቶች ግንባታ ላይ ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡ የክፍያ መመሪያዎቹ በውሃ' በትምህርትና በጤና ቢሮዎች ወይም በዞንና በወረዳ ጽ//ቤቶች ሊዘጋጁ ይችላሉ፡፡

ነገር ግን አርቴዣኖች ለስልጠና ከተመረጡበት/ከተመለመሉበት ጊዜ ጀምሮ በጥቃንና አነስተኛ ተቋምነት የሚያደራጁ ክልሎች አሉ በእነዚህ ክልሎች ውስጥ አብዛኛዎቹ አርቴዣኖች የተደራጁና ክልሎቹም በእነዚን የተደራጁ ተቋማት ለግንባታ ስራ እያወዳደሩ/እያጫረቱ መስጠት የተለመደ አሰራር ነው፡፡ ስለዚህ እንደዚህ ዓይነት አሰራሩን ተግባራዊ እያደረጉ ያሉ ክልሎች በግልም ሆነ በማህበር የግንባታ ፈቃድ የሌላቸውን አርቴዣኖች በግንባታ እንዲያጫርቱም ሆነ እንዲያሰማሩ አይገደዱም፡፡

## 6.2.1.2) ቀድሞ በተዘጋጀ የቁርጥ የግንባታ ነጠላ ዋጋን በመጠቀም የግንባታ ጉልበት ውል አሰጣጥ

በአሁን ሰዓት በኢትዮጲያ የግንባታ ስራዎችን ለስራው ብቃት ላላቸው ተቋራጮች የቁርጥ ነጠላ ዋጋ (የክፍያ መመሪያ) በመጠቀም የግንባታ ስራዎችን ማሰራት የተለመደ ነው፡፡ በቅርብ ጊዜ የውሃ' መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስተር የግንባታ ስራ ፈቃድ ያላቸው ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማትና የግል ተቋራጮችን በቁርጥ ዋጋ ውል ለማሰረት የሚያስችል መመሪያ በማዘጋጀት ለክልሎች አሰራጭቷል፡፡ ይህ አሰራር በኮዋሽ ፕሮጀክት በአማራ ክልል ለውሃ ጣቢያና ለተቋማት መጸዳጃ ቤቶች ግንባታ በሰፊው የተለመደ ነው፡፡ ስለዚህ ቅድሚያ የተዘጋጀ የቁርጥ ነጠላ ዋጋዎችን በመጠቀም የግንባታ ስራዎችን ለአርቴዣኖች' ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት እንዲሁም ለግል ተቋራጮች እንደሚከተለው ማዘጋጀትና መጠቀም ይቻላል፡፡

- ለውሃ ጠቢያዎች ግንባታ የቁርጥ ነጠላ ዋጋ (የክፍያ መመሪያው) በክልሉ የውሃ ቢሮ ተዘጋጅቶ ለየወረዳው የውሃ ጽ/ቤቶች እንዲጠቀሙበትና ማሻሻል/መከለስ አስፈላጊ ሲሆን ጽ/ቤቱ ለቢሮው እንዲያሳውቅ በማሳሰብ የክፍያ መመሪያው ይላካል፡፡

- ለትምህርት ተቋማት አገልግሎት ለሚገነቡ መጸዳጃ ቤቶች ግንባታ የቁርጥ ነጠላ ዋጋ/የክፍያ መመሪያው በክልሉ ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ ለየወረዳው ትምህርት ጽ/ቤቶች እንዲጠቀሙበትና ማሻሻል/መከለስ አስፈላጊ ሲሆን ጽ/ቤቱ ለቢሮው እንዲያሳውቅ በማሳሰብ የክፍያ መመሪያው ይላካል፡፡

- ለጤና ተቋማት አገልግሎት ለሚገነቡ መጸዳጃ ቤቶች ግንባታ የቁርጥ ነጠላ ዋጋ/የክፍያ መመሪያው በክልሉ ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ ለየወረዳው ትምህርት ጽ/ቤቶች እንዲጠቀሙበትና ማሻሻል/መከለስ አስፈላጊ ሲሆን ጽ/ቤቱ ለቢሮው እንዲያሳውቅ በማሳሰብ የክፍያ መመሪያው ይላካል፡፡

በቁርጥ ነጠላ ዋጋ ውል ወቅት የሚገነቡት የውሃ ጣቢያዎችና የተቋማት መጸዳጃ ቤቶች ለግል ተቋራጮች' ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት እንዲሁም የግንባታ ፈቃድ ለሌላቸው ግለሰብ አርቴዛኖች (በዚህ መመሪያ ንኡስ ክፍል 6.2.1.1. ላይ የተቀመጠውት ሁኔታዎች ሲገጥሙ) የወረደው ውሃ ጽ/ቤት' የትምህርት ጽ/ቤት ወይም የጤና ጽ/ቤት እንደ ፕሮጀክቶቹ ዓይነት' እንደሚገነቡበት ቦታ እንዲሁም እንደተቋራጩና ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋሙ ወይም እንደአርቴዣኑ ብቃት ሊያከፋፍሏቸው ይችላሉ፡፡

## 6.2.2) በመወዳደሪያ ሀሳብ መመየቂያ የሚፈጸም ግዥ

የእቃዎች' የግንባታ ጉልበትና ሌሎች አገልግሎቶችን በመወዳደሪያ ሀሳብ መመየቂያ ግዥ መፈጸም የሚቻለው በሚከተሉት ሁኔታዎች  ነው፡፡

**በአንድ ጊዜ የሚገዛው እቃ' የግንባታ ጉልበት ወይም አገልግሎት ዋጋ ግምት ከብር 10,000 በላይ ሲሆን'**

- ቢያንስ 3 /ሶስት/ አቅራቢዎች መጋበዝና የዋጋ ማቅረቢያውን ሞልተው መመለስና መወዳደር ይኖርባቸዋል፡፡

**ሌሎች አስፈላጊ ሁኔታዎች**

- ዋሸኮው የዋጋ ማቅረቢያ መጠየቂያው ላይ ፍላጎቱን የሚገልጽ መግለጫና የሚገዛውን እቃ ወይም አገልግሎት ጥራት' ብዛት' የማቅረቢያ ጊዜና ሌሎች ሁኔታዎች የሚያብራራ መግለጫ ማዘጋጀት አለበት፡፡

- ዋሸኮው ከዚህ በፊት ካለው ልምድ አቅራቢው/ዎቹ አነስተኛ ዋጋ በማቅረብ የታወቀ/ቁ ካልሆነ/ኑ በስተቀር ተመሳሳይ አቅራቢዎችን ሁል ጊዜ ዋጋ እንዲቀርቡ መጠየቅ አይመከርም፡፡

- ዋሸኮው ተወዳዳሪዎቹ የዋጋ ማቅረቢያውን በአግባቡ ሞልተው እንዲመልሱ በቂ የዋጋ መሙሊያ ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ይህም ዋጋ መሙሊያው ለተወዳዳሪዎቹ ከተሰጠበት ጀምሮ ከአንድ ቀን እስከ አምስት መቁጠሪያ ቀናት ሊሆን ይችላል፡፡

- የዋጋ ማቅረቢያውን ሞልተው ከመለሱት ተጫራቾች ውስጥ በዋጋ ማቅረቢያ መጠየቂያ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች አሟልቶ ዝቅተኛ ዋጋ ላቀረበው ተጫራች የግዥ ወይም የስራ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

- ተጫራቾቹ የሚያቀርቡት ዋጋ የማይለወጥ መሆኑን በዋጋ ማቅረቢያ መጠቂያው ላይ ሊገለጽላቸው ይገባል፡፡ በዋሸኮውና በተጫራቾች መካከል የዋጋ ድርድር ማድረግ አይፈቀድም፡፡

- ዋሸኮዎች በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ የተጋበዙትን ተጫራቾች ማንነት ለማንም ማሳወቅ የለባቸውም/በሚስጥር መያዝ አለባቸው፡፡

- የወራዳው ዋሽ ቡድን/የወረዳው ውሃ ጽ/ቤት በየጊዜው የገበያ ጥናት  በማድረግ ለዋሸኮው ውሳኔ የሚያግዝ የአገልግሎትና እቃዎችን ዋጋ መረጃ መስጠት ያስገልጋል፡፡

## 6.2.1) ግልጽ ጨረታ

ለእቃዎችና ለግንባታ የሚሆን ጉልበትም ሆነ ሌሎች አገልግሎቶችን ለመግዛት የግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴን በሚከተሉት ሁኔታዎች መጠቀም ይቻላል፡፡ ይህን የግዥ ዘዴ መጠቀም ግን አስገዳጅ አይደለም፡፡

- ***ማንኛውንም  የዋጋ ግምት ያለው የአንድ ጊዜ ግዥ ዋሽኮው የግልጽ ጨረታ ግዥን መጠቀም ከዋጋና ከጥራት አንጻር የሚገዙት እቃዎችና አገልግሎቶች ለፕሮጀክቱ ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎ ሲታሰብና ለግልጽ ጨረታ ግዥው የሚወስደው ጊዜ በፕሮጀክቱ ግንባታ ላይ መጓተት/ተጽእኖ እንደማያስከትል ሲታመንበት ነው፡፡***

***ሌሎች አስፈላጊ ሁኔታዎች***

- ዋሽኮው በወረዳው ፋይናንስና ሌሎች አግባብ ባላቸው ጽ/ቤቶች በመታገዝ ግልጽ የሆነ የጨረታ ሰነድ ያዘጋጃል፡፡
- የጨረታ ማስታወቂያው ቢያንስ በወረዳውና በአጎራባች ወረዳዎች ዋና ከተሞች ላይ በግልጽ ማስታወቂያ መለጠፍ አለበት፡፡ ማስታወቂው በዞን ዋና ከተማና በክልሉ ከተማ ቢለጠፍም ጥሩ ይሆናል፡፡
- ዋሽኮው ተወዳዳሪዎቹ የጨረታ ሰነዱን በአግባቡ ሞልተው እንዲመልሱ በቂ ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ይህም ጊዜ ጨረታው በአየር ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ <u>ከ 10 መቁጠሪ ቀናት ያላነሰ</u> ቢቻል ደግሞ 15 ቀናት ቢሆን ይመረጣል፡፡ ጨረታውም ቢያንስ በወረዳውና በአጎራባች ዋና ከተማዎች በሚታወቁ የማስታወቂያ መለጠፊያ ቦታዎች መለጠፍ አለበት፡፡ ከተቻለ በዞንና በክልል ዋና ከቶሞችም ማስታወቂያውን መለጠፍ ጥሩ ነው፡፡
- ተጫራቾቹ የሚያቀርቡት ዋጋ የማይለወጥ መሆኑን በጨረታ ሰነዱ ላይ ሊገለጽላቸው ይገባል፡፡ በዋሽኮውና በተጫራቾች መካከል የዋጋ ድርድር ማድረግ አይፈቀድም፡፡
- አንድ የጨረታ ሰነድ ብቻ ቢቀርብና የተሟላ ቢሆን ዋሽኮው ጨረታውን መገምገምና ጨረታውን ለዚሁ ተጫራች መስጠት ይችላል፡፡ ነገር ግን ጨረታው በጨረታ ማስታወቂያ መስፈርቱ መሰረት በስፋት የወጣና ሌሎች ተጫራቾችን ከመጫረት የሚያግድ ሁኔታ አለመኖሩ' የጨረታ ዋጋው ከወቅቱ የገበያ ዋጋ ወይም ከተቀመጠው ግምት ጋር የተጣጣመና ጨረታው በጨረታ ሰነድ ላይ የተገለጸውን የቴክኒክ ዝርዝሮችና ሌሎች የተጠቀሱትን ሁኔታዎችን ማሟላት አለበት፡፡
- የጨረታ ሰነዱን ሞልተው ከመለሱት ተጫራቾች ውስጥ በሰነዱ ላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች አሟልቶ ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበው ተጫራች የጨረታው አሸናፊ ይሆናል፡፡
- የወራዳው ዋሽ ቡድን/የወረዳው ውሃ ጽ/ቤት በየጊዜው የገበያ ጥናት  በማድረግ ለዋሽኮው ውሳኔ የሚያግዝ የአገልግሎትና እቃዎችን ዋጋ መረጃ መስጠት ያስገልጋል፡፡

## 6.3) የስራዎች ግዥ/የሙሉ የግንባታ ስራዎች ግዥ

### 6.3.1) ከአንድ አቅራቢ የሚፈጸም ግዥ

የስራዎች ግዢ/የሙሉ የግንባታ ስራዎች ግዥ ከአንድ አቅራቢ መፈጸም የሚቻለው በሚከተሉት ሁኔታዎች ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ዋሽኮው በሁኔታዎቹ ላይ በመወያየት ውሳኔውን በቃለ ጉባኤ በመያዝ የዋሽኮው ዉሳኔ ቃለጉባዔ በወረዳው ዋሽ ቡድን መጽደቅ አለበት፡፡

- **በአንድ ጊዜ የሙሉ የግንባታ ስራዎች ዋጋ ግምት ብር 250,000 እና ከዚያ በታች ሁኖ ከሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ ቢያንስ አንዱ ሲከሰት/ሲገጥም፡፡**
    - በመወዳደሪያ ሀሳብ መመየቂያ የሚፈጸም ግዥ **ቢያንስ ሁለት ጊዜ ተሞክሮ** በቂ ተወዳደሪ ያልተገኘ ወይም ፕሮፎርማውን ሞልተው የመለሱ እጩ ተወዳዳሪዎች የገዥውን ፍላጎት ማሟላት ሳይችሉ'
    - ግዥው በአስቸኳይ ካልተፈጸመና ስራው ካልተጀመረ/ካልተከናወነ ፕሮጀክቱ ከፍተኛ ችግርና ጉዳት ላይ የሚሆን/የሚወድቅ መሆኑ ሲታመንበት፡፡ ለምሳሌ በአካባቢው ስራው ላይ አደጋ ሊስከትል የሚችል ከፍተኛ ዝናብ መከሰት'
    - በቴክኒክ ምክንያት ግንባታው ሊያከናወን የሚችለው በአንድ ድርጅት ብቻ ከሆነና ድርጅት ጥራትና የቴክኒክ ችሎታው ከሌሎች በተመሳሳይ መስክ ከሚሰሩ ድርጅቶች ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ መሆኑ ሲታመንበትና ድርጅቱ የግንባታ ስራውን በሚፈለገው ጥራትና ተቀባይነት ባለው የገበያ ዋጋ ማከናወን እንደሚችል ሲታመንበት'

**በአንድ ጊዜ የሙሉ የግንባታ ስራዎች ዋጋ ግምት ከብር 250,000 በላይ ሁኖ ከሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ ቢያንስ አንዱ ሲከሰት/ሲገጥም፡፡**

- የግልጽ ጨረታ ግዥ ሁለት ጊዜ ተሞክሮ ምንም ተጫራች መቅረብ ካልቻለ ወይም የቀረቡት ተጫራቾች በጨረታ ሰነዱ ላይ የተቀመጡትን መመዘኛዎች የማያሟሉ ከሆነ እና ጨረታውን ለሶስተኛ ጊዜ መውጣት ወይም በግዥ መጠየቂያ ግዥውን ለማከነውን መሞከር በመጀመሪያ ከወጡት ሁለት የጨረታ ሂደቶች/ውጤቶች በመነሳት በቂ ተጫራቾች ሊያመጣ አይችልም የሚል ግምት ካለ ይህ ጉዳይ በወረዳው ዋሽ ቡድን ከጸደቀ ግዥውን ከአንድ አቅራቢ መፈጸም ይቻላል፡፡

**ከአንድ አቅራቢ በሚፈጸም ግዥ ወቅት ትኩረት የሚሹ ሌሎች ሁኔታዎች**

- የወረዳው ዋሽ ሴክተር መስሪያ ቤቶች ከዞን ሴክተር መስሪያ ቤታቸው ወይም በቢሮአቸው በመታገዝ ዋሽኮዎች በተጫራቾች የሚቀርበውን ዋጋ አግባብነት ለማገጋገጥ እንዲችሉ ከጨረታ በፊት ዋጋ ግምት ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡

- ዋሽኮዎች በወረዳ ዋሽ ሴክትር ባለሙያዎች በመታገዝ የሚሰራውን ስራ ዲዛይን' የስራ ዝርዝር መግለጫ' የእያንዳንዱ ስራ መጠን እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን ያካተተ የጨረታ ሰነድ በማዘጋጀት ለተወዳዳሪዎች ዋጋን ሞልቶ እንዲያቀርብ ለተወዳዳሪው ይሰጣሉ፡፡

- በዚህ ጊዜ ዋሽኮዎች ከተጫራቹ ጋር ውል ከመያዛቸው በፊት የተጫራቹ የስራ ልምድ' ያቀረበው ዋጋ አግባብነት' ስራውን በወቅቱ ለማጠናቀቅ እንደሚችልና የመሳሉትን ነገሮች ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

- ዋሽኮዎች ዋጋን ቀጥታ ከአንድ ተጫራች መጠየቅና ከተጫራቹ ጋር በዋጋና ሌሎች የውል ሁኔታዎች ላይ (ለምሳሌ የውል ማጠናቀቂ ጊዜ) በነጻነት መደራደር ይችላሉ፡፡

## 6.3.2) በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ የሚፈጸም ግዥ

የስራዎች ግዥ/የሙሉ የግንባታ ስራዎች ግዥ በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ መፈጸም የሚቻለው በሚከተሉት ሁኔታዎች ነው፡፡

**በአንድ ጊዜ የሙሉ የግንባታ ስራዎች ዋጋ ግምት ብር 250,000 እና ከዚያ በታች ሲሆን፡፡**

- ቢያንስ 3 /ሶስት/ አቅራቢዎች መጋበዝና የዋጋ ማቅረቢያውን ሞልተው መመለስና መወዳደር ይኖርባቸዋል፡፡

**ሌሎች አስፈላጊ ሁኔታዎች**

- የወረዳው ዋሽ ሴክተር መስሪያ ቤቶች ከዞን ሴክተር መስሪያ ቤታቸው ወይም በቢሮአቸው በመታገዝ ዋሽኮዎች በተጫራቾች የሚቀርበውን ዋጋ አግባብነት ለማገጋገጥ እንዲችሉ ከጨረታ በፊት ዋጋ ግምት ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡

- ዋሽኮዎች በወረዳ ዋሽ ሴክትር ባለሙያዎች በመታገዝ የሚሰራውን ስራ ዲዛይን' የስራ ዝርዝር መግለጫ' የእያንዳንዱ ስራ መጠን እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን ያካተተ የጨረታ ሰነድ በማዘጋጀት ለተወዳዳሪዎች ዋጋን ሞልቶ እንዲያቀርብ ለእጩ ተወዳዳሪው ይሰጣሉ፡፡

- ዋሽኮው ተወዳዳሪዎቹ የዋጋ ማቅረቢያውን በአግባቡ ሞልተው እንዲመልሱ በቂ የዋጋ መሙሊያ ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ይህም ዋጋ መሙሊያው ለተወዳዳሪዎቹ ከተሰጠበት ጀምሮ ከአንድ ቀን እስከ ሰባት መቁጠሪያ ቀናት ሊሆን ይችላል፡፡

- የዋጋ ማቅረቢያውን ሞልተው ከመለሱት ተጫራቾች ውስጥ በዋጋ ማቅረቢያ መጠየቂያ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች አሟልቶ ዝቅተኛ ዋጋ ላቀረበው ተጫራች የግዥ ወይም የስራ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

- ተጫራቾቹ የሚያቀርቡት ዋጋ የማይለወጥ መሆኑን በዋጋ ማቅረቢያ መጠቂያው ላይ ሊገለጽላቸው ይገባል፡፡ በዋሽኮውና በተጫራቾች መካከል የዋጋ ድርድር ማድረግ አይፈቀድም፡፡

- ዋሽኮዎች በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ የተጋበዙትን ተጫራቾች ማንነት ለማንም ማሳወቅ የለባቸውም/በሚስጥር መያዝ አለባቸው፡፡

## 6.3.3) የግልጽ ጨረታ ግዥ

የስራዎች/የግንባታ ስራዎች ሙሉ ውል የግልጽ ጨረታ ተግባራዊ የሚደረገው በሚከተሉት ሁኔታዎች ነው፡፡

**የአንድ ግዜ ግዥ ዋጋ ግምት ከብር 250,000 በላይ ሲሆን፡፡**

**ሌሎች አስፈላጊ ሁኔታዎች**

- የወረዳው ዋሽ ሴክተር መስሪያ ቤቶች ከዞን ሴክተር መስሪያ ቤታቸው ወይም በቢሮአቸው በመታገዝ ዋሽኮዎች በተጫራቾች የሚቀርበውን ዋጋ አግባብነት ለማረጋገጥ እንዲችሉ ከጨረታ በፊት የዋጋ ግምት ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡

- ዋሽኮዎች በወረዳ ዋሽ ሴክትር ባለሙያዎች በመታገዝ የሚሰራውን ስራ ዲዛይን' የስራ ዝርዝር መግለጫ' የእያንዳንዱ ስራ መጠን እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን ያካተተ የጨረታ ሰነድ በማዘጋጀት ለተወዳዳሪዎች ዋጋን ሞልተው እንዲያቀርቡ ይሸጣሉ፡፡

- የጨረታ ጥሪው/ማስታወቂያው ለብዙ ተጫራቾች ሊደርስና ሊታይ በሚችል መልኩ ሁኖ ከአካባበቢውና ከአካባቢው ውጭ በሆኑ ተጫራቾች ሊያነቧቸው በሚችሉ ቦታዎች (በአጎራባች ወረዳዎች' በዞን ዋና ከተማና ከተቻለም ከክልል ዋና ከተማ) ሊለጠፉ ይገባል፡፡ ጨረታ ማስታወቂያውን የመነበብ እድል ለማስፋት ማስታወቂያዎቹን በዋሽ ሴክተር ጽ/ቤቶች ግጥር ግቢዎች መለጠፍም ያስፈሊጋል ፡፡ እንደየስራዎቹ ዓይነትና ዋጋ እንዲሁም ለስራው የሚያስፈልጉ ተጫራቾች ሊገኙባቸው የሚችሉ ቦታዎችን ለማስፋት ጨረታው ቢያንስ አንድ ጊዜ በአገር አቀፋዊ እና/ወይም ክልላዊ ሽፋን ባላቸው ጋዜጣዎች ላይ ቢወጣ ጥሩ ነው፡፡ አገራቀፋዊ ጋዜጣ ቢያንስ **አዲስ ዘመን**ን ሲይዝ ክልላዊ ጋዜጣዎች ደግሞ ለምሳሌ በአማራ ክልል **በኩር** ጋዜጣና በትግራይይክልል **ሜካለህ** የመሳሰሉትና ጋዜጣዎች ያካትትታል፡፡ ይህን ለመወሰን የወረዳው ዋሽ ቡድን አስፈላጊውን መረጃና ምክር ለዋሽኮው መስጠት አለበት፡፡ የወረዳ ዋሽ ቡድኑም በዚህ ጉዳይ ላይ በቂ መረጃ ከሌለው የውሃ ቢሮውን መጠየቅ ይችላል፡፡ ለግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ የተጠቀሙበትን ዘዴና ይህን ለመጠቀም የወሰኑበትንም ምክንያት ዋሽኮዎች በቃለጉባኤ መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡ የጨረታ ማስታወቂያው የሚወጣው የጨረታ ሰነዱ በተዘጋጀበት ቋንቋ ነው፡፡

- ዋሽኮው ተወዳዳሪዎቹ የዋጋ ማቅረቢያውን በአግባቡ ሞልተው እንዲመልሱ በቂ የዋጋ መሙሊያ ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ይህም ዋጋ ጨረታው በአየር ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ <u>ከ 15 መቁጠሪ ቀናት ያላነሰ</u> ቢቻል ደግሞ 21 ቀናት ቢሆን ይመረጣል፡፡

- ተጫራቾቹ የሚያቀርቡት ዋጋ የማይለወጥ መሆኑን በጨረታ ሰነዱ ላይ ሊገለጽላቸው ይገባል፡፡ በዋሽኮውና በተጫራቾች መካከል የዋጋ ድርድር ማድረግ አይፈቀድም፡፡

- አንድ የጨረታ ሰነድ ብቻ ቢቀርብና የተሟላ ቢሆን ዋሽኮው ጨረታውን መገምገምና ጨረታውን ለዚሁ ተጫራች መስጠት ይችላል፡፡ ነገር ግን ጨረታው በጨረታ ማስታወቂያ መስፈርቱ መሰረት በስፋት የወጣና ሌሎች ተጫራጮችን ከመጫረት የሚያግድ ሁኔታ አለመኖሩ' የጨረታ ዋጋው ከወቅቱ የገበያ ዋጋ ወይም ከተቀመጠው ግምት ጋር የተጣጣመና ጨረታው በጨረታ ሰነድ ላይ የተገለጸውን የቴክኒክ ዝርዝሮችና ሌሎች የተጠቀሱትን ሁኔታዎችን ማሟላት አለበት፡፡

- የገዙትን የጨረታ ሰነድ ዋጋ ሞልተው ከመለሱት ተጫራቾች ውስጥ በጨረታ ሰነዱ ላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች አሟልቶ ዝቅተኛ ዋጋ ላቀረበው ተጫራች የግዥ ወይም የስራ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

## 6.3.3.1) ስለግልጽ ጨረታ ግዥ ተጨማሪ ጉዳዮች

ዋሽኮዎች ማንኛውንም ግዥ በወረዳ ባለሙያዎች በመታገዝ በደንብ በታቀደና በግልጽ ጨረታ ቢያከናወኑ ጥሩ ይሆናል፡፡ ነገር ግን በዚህ መመሪያ ላይ የተገለጹት ሁኔታዎች ሲሟሉ ወይም ሲያስገድዱ ዋሽኮዎች የመረጡበትን ምክንያቶች በቃለጉባኤ በመያዝ ከአንድ አቅራቢ ወይም በዋጋ መጠየቂያ በሚፈጸም የግዥ ዘዴ በመጠቀም ግዢውን መፈጸም ይችላሉ፡፡ ግዥዎች በግልጽ ጨረታ በሚከናወኑበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

ሀ) **የጨረታ ሰነድ**

የጨረታ ሰነዱ በተጫራቾች መካከል የተሟላ' ገለልተኛና በጨረታው አላማ ላይ ብቻ የተመሰረተ ውድድር ሊያደርጉ እንዲችሉ በቂና ግልጽ የሆኑ መረጃዎችን በያዘ መልኩ መዘጋጀት አለበት፡፡ የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ቢያንስ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡፡

- የጨረታ ሰነድ ለማዘጋጀትና ለማቅረብ አስፈላጊ የሆኑ የተጫራቾች መመሪያ
- የስራው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫዎች
- የስራዎችን መጠንና ዝርዝር የሚያሳይ የዋጋ መሙሊያ ቅጽ

- የጨረታ ሰነድ ሽያጭ
- የጨረታ ሰነዶች አስተሻሸግ
- በጨረታ ሰነድ ላይ ስለሚደረግ ማሻሻያ
- ጨረታው የሚካሄድበት ቋንቋ
- ጨረታው ጸንቶ የሚቆይበት ቀን
- የጨረታ ማስከበሪው መጠንና የሚቀርብበት ፎርማት ወይም ዓይነት
- የመጫረቻ ሰነድ ስለማቅረብና ስለመረከብ
- ጨረታን ስለመክፈት
- የመጫረቻ ሰነዶችን ስለመመርመርና ስለመገምገም
- ስለድጋሚ ጨረታ
- ስለጨረታው ማብራሪያ የሚጠየቅበት ሂደትና ጥያቄው የሚቀርብበት አድረሻ
- በሚስጥር ስለሚያዙ ጉዳዮች/አሰራሮች
- ተጫራቹን ከጨረታ ውጭ ስለሚያደርጉ ሁኔታዎች
- የውል ማስከበሪያ መጠንና የሚቀርብበት ፎርማት ወይም ዓይነት
- የቅድሚያ ክፍያው መጠንና የክፍያው ዋስትና የሚያቀርብበት ፎርማት ወይም ዓይነት
- አሸናፊነትን ስለመግለጽና ውል ስለመፈራረም

ለ) የጨረታ ጥሪ

ከላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች የያዘ የጨረታ ሰነድ ከተዘጋጀ በኋላ የጨረታ ማስታወቂያው በሚከተለው ሁኔታ አየር ላይ ይውላል፡፡

የጨረታ ጥሪው/ማስታወቂያው ለብዙ ተጫራቾች ሊደርስና ሊታይ በሚችል መልኩ ሁኖ ከአካባበቢውና ከአካባቢው ውጭ በሆኑ ተጫራቾች ሊያነቧቸው በሚችሉ ቦታዎች (በአጎራባች ወረዳዎች' በዞን ዋና ከተማና ከተቻለም ከክልል ዋና ከተማ) ሊለጠፉ ይገባል፡፡ እንደየስራዎቹ ዓይነትና ዋጋ እንዲሁም ለስራው የሚያስፈልጉ ተጫራቾች ሊገኙባቸው የሚችሉ ቦታዎችን ለማስፋት ጨረታው ቢያንስ አንድ ጊዜ በአገር አቀፋዊ እና/ወይም ክልላዊ ሽፋን ባላቸው ጋዜጣዎች ላይ ቢወጣ ጥሩ ነው፡፡ ይህን ለመወሰን የወረዳው ዋሽ ቡድን አስፈላጊውን መረጃና ምክር ለዋሽኮው መስጠት አለበት፡፡ የወረዳ ዋሽ ቡድኑም በዚህ ጉዳይ ላይ በቂ መረጃ ከሌለው የውሃ ቢሮውን መጠየቅ ይችላል፡፡ ለግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ የተጠቀሙበትን ዘዴና ይህን ለመጠቀም የወሰኑበትንም ምክንያት ዋሽኮዎች በቃለጉባኤ መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡ የጨረታ ማስታወቂያው የሚወጣው የጨረታ ሰነዱ በተዘጋጀበት ቋንቋ ነው፡፡

- የጨረታ ማስታወቂያው የሚከተሉትን መያዝ አለበት
    - ግዥውን የሚፈጽመው ዋሽኮ ስምና አድራሻ
    - የእቃውና የአገልግሎቱ መጠንና የሚቀርብበት ቦታ ወይም የግንባታ ስራው ቦታ አጭር መግለጫ
    - የጨረታ ሰነድ ለማግኘት መሟላት ስለሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች እና የጨረታ ሰነዱ ስለሚገኝበት ቦታ
    - የጨረታ ሰነዱ የሚሸጥበት ዋጋ
    - የጨረታ ማስከበሪው መጠንና የሚቀርብበት ፎርማት ወይም ዓይነት

- ተጫራቾች የጨረታ ሃሳባቸውን የሚያቀርቡበት/የሚያዘጋጁበት ቋንቋ

- የጨረታ መወዳደሪያ ሃሳቡ/ሰነዱ የሚቀርብበት ቦታና ጨረታው የሚከፈትበት ቀን

- ዋሽኮው አሸናፊውን ይፋ ከመደረጉ በፊት ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ

## 7. በውክልና የሚፈጸሙ ግዥዎች

ዋሽኮው በዋጋ መጠየቂያ/በፕሮፎርማ ወይም በግልጽ ጨረታ የመፈጸሙ ግዥን የመፈጸም የአቅም ውስንነት ካለበት ምክንቶቹን በመግለጽ የግዥ ሂደቱን እንዲያከናውንለት የወረዳው ዋሽ ቡድንን መወከል ይችላል፡፡ የወረዳው ዋሽ ቡድን ውክልናውን ተቀብሎ ጨረታውን ካወጣ ቢያንስ የዋሽኮው ሰብሳቢና ጸሃፊው የጨረታ ሰነዱ ሲከፈት መገኘት አለባቸው፡፡ አሸናፊው ከተለየም በኋላ ከአሸናፊው ተጫራች ጋር ውል የሚፈርመው የዋሽኮው ሰብሳቢ ይሆናል፡፡ በተለያዩ ምክንቶች ዋሽኮው ውሉን መፈረም የማይችል ከሆነ የወረዳው ዋሽ ቡድንን ውሉን እንዲፈርምለት በመወከል ቡድኑ ውሉን ከአሸናፊው ተጫራች ጋር ሊፈርም ይችላል፡፡

በዋሽኮው የተወከለው የወረዳው ዋሽ ቡድን ጨረታውን የማውጣት የአቅም ውስንነት ካለበት ከዋሽኮው ተሰጠውን ውክልና በመጥቀስ የዞኑ ውሃ መምሪያን ወይም የውሃ ቢሮን መወከል ይችላል፡፡ የዞኑ መምሪያም አቅም ከሌለው ውሃ ቢሮውን መወከል ይችላል፡፡

**በዋሽኮው የሚሰጠው ውክልናም የሚከተለውን ሂደት የተከተለ መሆን አለበት፡፡**

- ውክልናው የሚሰጠው ወረዳው/ዞኑ/ቢሮው የግዥውን ሂደት ከመጀመሩ በፊት መሆን አለበት፡፡
- ዋሽኮው ውክልናውን የሚሰጠው በጽሁፍ ነው፡፡
- በውክልናው ደብዳቤ ላይ ዋሽኮው ለወረዳው ዋሽ ቡድን የወከላቸው ተግባራት በዝርዝርና ግልጽ ሁነው መቀመጥ አለባቸው፡፡
- ዋሽኮው ቡድኑን የወከለበት ምክንያቶችም ውክልናው ደብዳቤ ላይ በግልጽ መቀመጥ አለባቸው፡፡

በተቻለ መጠን በማንኛውም ዋሽኮው በወከለው ግዥ ወቅት ስራው ከተሰራና የክፍው ሰነድ ስራውን ባከናወነው ድርጅት ወይም ግለሰብ ከተዘጋጀ በኋላ ክትትል ባደረገው መስሪያ ቤት ባለሙያ ከተረጋገጠ በኋላ በዋሽኮው ሰብሳቢ ጸድቆ ክፍያው ከዋሽኮው ሂሳብ ወጪ በመሆን ለድርጅቱ ወይም ለግለሰቡ ይከፈላል፡፡

አንዳንድ ጊዜ በሞተር ሀይል ለሚሰሩ የውሃ ማከፋፈያ መስመሮች እና የመለስተኛ/የጥልቅ ውሃ ጉድጓድ ቁፋሮና ግንባታዎቹን ለማስተዳደር የሚያስፈልገው የቴክኒክ ብቃት' አንድ ጉድጓድን በተናጠል የሚቆፍር ድርጅት የማግኘት እድሉ በጣም አናሳ በሆነበት እንዲሁም ስራው ከተሰራ በኋላ በአንድ ጊዜ ሊከፈል የሚችለው ክፍያ መጠን ብዙ ሊሆን ስለሚችልና ይህን ተገንዘቦ ዋሽኮው ይህንን የማድረግ አቅም ውስንነት እንዳለበት ከተረዳና የወረዳ ዋሽ ቡድኑን ክፍያ እንዲፈጽምለት በውክልና ደብዳቤው ላይ በግልጽ ካስቀመጠ እንዲሁም ቡድኑ የውሃ ቢሮውን ከወከለ የተወከለው አካል በእንዳንዱ በሚዘጋጀው ክፍያ ላይ የዋሽኮው ሰብሳቢ ክፍያውን ከሚፈጽመው አካል ጋር በጋራ በማጽደቅ ክፍያውን የተወከለው አካል ስራውን ላከናወነው ግልሰብ ወይም ድርጅት ክፍያውን መክፈል ይችላል፡፡ በዚህ ወቅት እያንዳንዱ ክፍያ በዋሽኮው ከጸደቀ የተወከለው አካል ክፍያውን መፈጸሙ የማህበረሰብ ፕሮጀክት ትግበራ አሰራርን እንደመጣስ አይቆጠርም፡፡

## 8. ከግንባታ የተረፉ እቃዎችን እንደ ስሚንቶና ፌሮ የመሳሉትን ስለመሸጥ

በተቻለ መጠን በግንባታ ወቅት የግንባታ ቁሳቁሶች እንዳይባክኑ ለማድረግ እንዲሁም ከግንባታ ሀኋላ ሊተርፉ የሚችሉ የግንባታ ቁሳቁሶች እንዳይኖሩ ለማድገር የሚገዙ ቁሳቁሶች መጠን ለስራው በሚያስፈልገው መጠን ብቻ እንዲሆኑ እስከአሁን ድራስ የወረዳው ባለሙያዎች ለዋሽኮዎች እያደረጉ ያለው የቴክኒክ ምክርና እገዛ መቀጠል አለበት፡፡ ነገር ግን በተለያዩ ምክንያቶች በተለይም የኢንዱስትሪ ውጤት የሆኑ እንደ ስሚንቶና ፌሮ የመሳሰሉት ቁሳቁሶች ከግንባታ በኋላ ሊተርፉ ይችላሉ፡፡ እነዚህና መሰል ቁሳቁሶች በሚተርፉበት ወቅት ዋሽኮው ቁሳቁሶቹን በመሸጥ የሽያጭ ሰነዱን በውሃ ጽ/ቤት በማወራረድ ገንዘቡን ወደ ወረዳው የማህበረሰብ ፕሮጀክት ትግበራ ሂሳብ ቁጥር/አካውንት ገቢ ማድረግ አለበት፡፡ የዚህን ገንዘብ አመላለስ የወረዳው የውሃ ጽ/ቤትና የወረዳው ብድርና ቁጠባ ተቋም በጋራ መስራትና ዋሽኮውን ማገዝ አለባቸው አለበለዚያ ግን የዋሽኮውም ሆነ በአጠቃላይ የወረዳው የሂሳብ አጠቃቀም ሪፖርት ላይ ከፍተኛ ችግር ሊፈጥር ይችላል፡፡ የሚተርፉት ቁሳቁሶችንም ለመሸጥ ዋሽኮው የሚከተላቸው የግዥ ዘዴዎች እንደሚከተለው ይሆናሉ፡፡

- ለሽያጭ የቀረቡት የግንባታ ቁሳቁሶች ዓይነትና መጠን ይዘጋጅና በአንድ ጊዜ ለሽያጭ የቀረቡት ቁሳቁሶች የዋጋ መጠን ብር 10,000 እና ከዚያ በታች ከሆነ ዋሽኮው ግዥውን ሊፈጽሙ ከሚችሉ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ጋር በመደራደር በተሻለ/በከፍተኛ ዋጋ መሸጥ ይችላል፡፡ ይህን ሂደት ለማገዝና ለመከታተል የወረዳው ማህበረሰብ ፕሮጀክት ትግበራ ተቆጣጣሪና አንድ የውሃ ጽ/ቤት ባለሙያ መኖር

አለባቸው፡፡

- በአንድ ጊዜ ለሽያጭ የቀረቡት ቁሳቁሶች የዋጋ መጠን ከብር 10,000 በላይ ሲሆን ዋሽኮው ሽያጩን የሚያከናውነው በዋና ከተሞችና በ ሌሎች የተሻሉ ቦታዎች የሚታይ ግልጽ ጨረታ በማውጣት ይሆናል፡፡ይህን ሂደት ለማገዝና ለመከታተል የወረዳው ማህበረሰብ ፕሮጀክት ትግበራ ተቆጣጣሪና አንድ የውሃ ጽ/ቤት ባለሙያ መኖር አለባቸው፡፡የግልጽ ጨረታውም ሂደት እንደሚከተለው ይሆናል፡፡
    - የጨረታ ማስታወቂውን በወረዳው ዋና ከተማና በተለያዩ ቦታዎች ላይ መለጠፍ
    - ቢያንስ ሶስት ተጫራቾች መጫረት ይኖርባቸዋል
    - አሸናፊ የሚሆነው ተጫራች ከፍተኛ ዋጋ ያቀረበው ተወዳዳሪ ነው፡፡

በሁለቱም የሽያጭ ዘዴዎች ወቅት ዋሽኮዎች የሽያጩን ዘዴ ለመወሰን ያደረጉት የስብሰባና ሽያጩ በተከናወነበት ወቅት ያደረጉት ስብሰባ ቃለ ጉባኤዎች ማዘጋጀት አለባቸው፡፡

ዋሽኮዎች የቁሳቁሶችን ሽያጭ የሚያከናውኑበት ደረሰኝ ስለሌላቸው በዚህ መመሪያ እዝል 1 ላይ የታየው እንደህጋዊ ደረሰኝ የሚያገለግል ቅጽ/ፎርማት ተዘጋጅቷል፡፡

## ኮዋሽ ፕሮጀክት ምእራፍ 3

### እዝል ፤. ዋሽኮዎች/ወመህ/የጤና ከሚቴዎች ከግንባታ የተረፉ የግንባታ ቁሳቁሶችን ሲሸጡ ገንዘብ የሚቀበሉበት ቅጽ/ደረሰኝ

ቀን ___________________

የደረሰኝ ቀ.. ______/2009_____

ቁሳቁሱን የሸጠው ዋሽኮ ስም___________________________________________________

ቁሳቁሱን የገዛው ግለሰብ/ድርጅት ስም__________________________________________________

| ተ.ቁ. | የቁሳቁሱ መጠሪያ | መለኪያ | መጠን | ነጠላ ዋጋ (ብር) | ጠቅላላ ዋጋ (ብር) |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| ጠቅላላ ዋጋ (ብር) | | | | | |

የገንዘቡ መጠን በአኃዝ_______________________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________________

ያዘጋጀው (የዋሽኮው ሂሳብ ሰራተኛ)_______________________________________

ያጸደቀው (የዋሽኮው ሰብሳቢ)_______________________________________

ገንዘቡን የተቀበለው (የዋሽኮው ገንዘብ ያዥ)_______________________________________

ማሳሰቢያ ፤. ይህ ደረሰኝ በሶስት ቅጅ የዘጋጃል፡፡ አንዱ ቅጅ ለገዥው' አንዱ ቅጅ ለውሃ ጽ/ቤት ሂሳቡ ሲወራረድ ሲሰጥ አንዱ ቅጅ ዋሽኮው ጋር ይቀራል፡፡

2. ዋሽኮዎች የሸጡበትን ሂሳብ በዚህ ደረሰኝ ሲወራርዱና ግንዘቡን ወደ ብድርና ቁጠባ ተቋሙ ለመመለስ ወደ ወረዳው ውሃ ጽ/ቤት ሲሄዱ የተረፉት ቁሳቁሶች እንዲሸጡ የተስማሙበትንና ግዥው ውሳኔ የተደረገበትን የስብሰባ ቃለ ጉባዔ ለውሃ ጽ/ቤቱ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡